የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፸፪
አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year, No.72
ADDIS ABABA, 16th May, 2016

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፰/፪ሺ፰ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፖርቹጋል ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር.............................................ገፅ ፱ሺ፷

**CONTENTS**

Proclamation No.948/2016

Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Portuguese Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation....................page 9060

አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፰/፪ሺ፰

**በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፖርቹጋል ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፖርቹጋል ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፮ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

**PROCLAMATION No. 948 /2016**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONVENTION BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE PORTUGUESE REPUBLIC FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME**

**WHEREAS,** a Convention for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income has been signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Portuguese Republic on the 15th of May 2013, in Addis Ababa

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said convention at its session held on the 14th day of April, 2016;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፖርቹጋል ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፵፰/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፖርቹጋል ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም  በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Portuguese Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No. 948/2016”.

**2. <u>Ratification of the Convention</u>**

The Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Portuguese Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed on the 15th day of May 2013 is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to implement the Convention in cooperation with the concerned government organs.

**4. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of May 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**
**REPUBLIC OF ETHIOPIA**